በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የዓለም ፍጻሜ

## *ክፍል ሁለት*


## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com


*ቦታ፦* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ግንቦት ፳፩ ፳፻፫ ዓ.ም.

# የግብረ ሥጋ “አብዮት” በዘመናችን

- መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ ቪዲዮ ጌሞች እና የሙዚቃ ቪዲዮዎች ያለ ተጽእኖ አላቸው፡፡

- በአሜሪካን አገር የሚገኝ አንድ የግብረ ኃይል ማኅበር በዚህ ዙሪያ ስላሉ እንቅስቃሴዎች ገልጧል፡፡

- ተላጽቆ ወይም ግብረ ሥጋ በራስ መተማመንን ከማሳጣቱም በላይ ለምግብ ፍላጎት መ1ደል ወይም መዛባትና ለሕይወት ቀውስ - መደበት- የልብ ሐዘን መከሰት ምክንያት ይሆናል፡፡

# የግብረ ሥጋ "አብዮት" ምሳሌዎች በዘመናችን

- የፖፕ አቀንቃኞች የሚለብሷቸው ስሜት ቀስቃሽ ልብሶች

- ወጣት ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠሩ ፊሽኔት ታይትን የመሳሰሉ ልብሶችን የለበሱ ታይቶች

- ከ10 ዓመት በላይ በሆኑ ወጣቶች እየተለበሱ ያሉ ቶንግስን የመሳሰሉ ልብሶች

- በአዋቂዎች የሚለበሱ የወጣት የልብስ ሞዴሎች

# የግብረ ሰዶማዊነት መከሰቻ ምክንያቶች

- በአባትና በልጅ መካከል የሚኖር ጤናማ ያልሆነ ግኑኝነት
- ይልቁኑ በወንዶች የሚፈጸሙ ግብረ ሥጋዊ ነውጦች ወይም ሙከራዎች
- ልቅ ለሆኑ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ፊልሞች መጋለጥ
- ተቃራኒ የሆኑ መንፈሳዊ ተጽእኖዎች (ግብረ ሰዶማዊ “ጳጳሳትንና ቀሳውስትን” መሾም)
- የመገናኛ ብዙኀን ተጽእኖ (ሁሉን የማቻቻል ሲባል የሚመጣ)
- የራስ ግላዊ ጠባይ፤ ጎጂ የሆነ አካላዊ ገጽታ
- ወደ ተቃራኒ ጾታ ለመቅረብ መፍራት ወይም አለመቻል

# ግብረ ሰዶማዊነትና መጽሐፍ ቅዱስ

- በብሉይ በሞት ያስቀጣ ነበር፡፡

- "ከሴትም ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ ጸያፍ ነገር ነውና፡፡" *ዘሌዋ 18፡22፡፡* "ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋል ፈጽመው ይገደሉ ደማቸው በላያቸው ነው፡፡" *ዘሌዋ 20፡13፡፡*

- "የማይጠፋውንም የእግዚአብሔር ክብር በሚጠፉ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ፡፡ ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኵስነት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ፡፡" *ሮሜ 1፡23-27*

# ግብረ ሰዶማዊነትና መጽሐፍ ቅዱስ

- "ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም። ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ ተብሎአልና። ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው። ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል። ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" _1ኛ ቆሮ 6:15-20።_

- "ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀራጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ" _1ኛ ቆሮ 6:9።_

- እነዚህ በንስሐ ካልተመለሱ አንዳቸውም የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።

- ከተመለሱ ግን "ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።" _1ኛ ቆሮ 6:11_ እንደተባለ ይደረግላቸዋል።

# ግብረ ሰዶማዊነትና መጽሐፍ ቅዱስ

- “ይኸውም፥ ለበደለኞችና ለማይታዘዙ፥ ለዓመጸኞችና ለኃጢአተኞች፥ ቅድስና ለሌላቸውና ለርኵሳን፥ አባትና እናትን ለሚገድሉ፥ ለነፍሰ ገዳዮችና ለሴሰኞች፥ ከወንድ ጋርም ለሚተኙ፥ በሰዎችም ለሚነግዱ፥ ለውሸተኞችም በውሸትም ለሚምሉ፥ የብሩክ እግዚአብሔርንም ክብር እንደሚገልጥ ለእኔ አደራ እንደ ተሰጠኝ ወንጌል የሆነውን ደኅና ትምህርት ለሚቃወም ለሌላ ነገር ሁሉ ሕግ እንደ ተሰራ እንጂ ለጻድቅ እንዳልተሰራ ሲያውቅ ነው።” *1ኛ ጢሞ 1፡9-10።*

- ቅዱስ ጳውሎስ ግብረ ሰዶማውያንን ከነፍሰ ገዳዮች፤ ከውሸተኞች፤ ሕግን ከማይጠብቁና እግዚአብሔርንም ከማያመልኩት ጋር አድርጎ ጽፎልናል፡፡

- “እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።” *ይሁ 7።*

# በጋብቻ ብቻ የሆነ የወንድና የሴት አንድነት

- “እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ፦ ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥ አለም። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።” *ማቴ19፡4-6።*

- “እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። … አዳምም ለእንስሳት ሁሉ፥ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ፥ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር። እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት። አዳምም አለ፦ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።” *ዘፍጥ 2፡7፤ ዘፍጥ 2፡20-23።*

- “እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንምሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።” *ዘፍጥ 1፡27-28።*

# ጋብቻ፤ ጌታችንና ቤተክርስቲያን

- *ሚስቶች፡-* “ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና። ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ።” *ኤፌ 5፡22-24።*

- *ባሎች፡-* “ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ። ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ።” *ኤፌ 5፡30-33*

# ማጠቃለያ

- - ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸልን በወንድና በሴት መካከል ብቻ የሆነውን ጋብቻን በማክበር የመጨረሻው ዘመን አንዱ ምልክት ከሆነው ግብረ ሰዶማዊነት ራሳችንን እንጠብቅ፡፡

- ከግብረ ሰዶማውያን ጋር የሚኖረን ግኑኝነትም ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ምንም መልእክት የማይተላለፍበት ልቅ የሆነ ግኑኝነታችን የኛን ስም ሊያጠፋ የሚችል ከመሆኑ በላይ እነርሱም ሁነታችንን ሲያዩ የያዙት የጥፋት ጎዳና የሚሻሻልና የሚታረም ነገር እንደሌለበት አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት #በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ ምስጉን ነው ፡፡; የሚለንም ለዚህ ነው፡፡*መዝ 1፡1፡፡*

- ቤተክርስቲያን በዚህ ችግር ውስጥ ሆነው ለመውጣት የሚፈልጉትን ሁሉ ንስሐ ገብተው እንዲስተካከሉ አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ ታደርግላቸዋለች፤ ከማድረግም አትቆጠብም፤ የምትቃወመውም ሰዎቹን ሳይሆን ሥራቸውን ነው፡፡

- በፍጻሜው ዘመን ከሚሆነው የኃጢአትና የጥፋት ሥራ ሁሉ የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት ይጠብቀን፡፡

# አርማጌዶን

- የመጊዶ አምባ ወይም የጦር ሠራዊት ሠፈር ማለት ነው፡፡
- ጥንት ለንግድም ሆነ ለጦርነት ዋነኛ መተላለፊያ ነበር፡፡
- ነቢይቱ ዲቦራና ባርቅ 900 የብረት ሠረገሎች የነበሩትን የከነዓን ንጉሥ ኢያቢስንና የሠራዊቱን አለቃ ሲሣራን በዚህ ቦታ ጦርነት ገጥመው በእግዚአብሔር ኃይል አሸንፈዋል፡፡
- በርካታ ጦርነቶች በተካሄዱበት በዚህ ቦታ የመጨረሻው ጦርነት እንደሚካሄድበት በራእየ ዮሐንስ ተገልጿል፡፡ ራእ 16፡13-16፤ 20፡7-9፡፡



- *በሥዕሉ የምናየው ከአርማጌዶን ሰሜን ምስራቅ በኢይዝራኤል ሸለቆ ወደ ደብረ ታቦር ስንመለከት ያለውን እይታ ነው፡፡*
- አንዳንድ አጥኚዎች አርማጌዶን ጥንታዊቱን ኢየሩሳሌምን፤ የቴልአቪቭን ከተማ፤ ሐዞርን፤ ቤርሳቤህ፤ የባዢን "ቅዱስ ሥፍራ"፤ ጢሮስን፤ የሜዴትራንያን ባህር ዳርቻዎችን ያካትታል ይላሉ፡፡
- ጦርነቱ በጽድቅ አገልጋዮችና በክፋት ሠራዊት መካከል የሚካሄድ መንፈሳዊ ጦርነት ሲሆን እስካሁን ተሰምቶ የማይታወቅ ታላቅ እልቂት የሚሆንበት ነገሥታትንም ሁሉ የሚያሳትፍ ጦርነት ነው፡፡
- ወደ ቅድስቲቱ አገር የሚተመውን የክፋት ሠራዊት የሚመራው ጎግ ወይም ማጎግ ነው፡፡ሕዘ 38፡2-16፡ ይህም ከያፌት ሦስት ልጆች አንዱ ነው፡፡ አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ "መስኮቦች" ብለው ተርጉመዋል፡፡ አንዳንዶች ለቻይና ይሰጣሉ፡፡
- በአጠቃላይ አእላፋት ሠራዊት አስከትሎ ጎግ ማጎግ በክርስቲያኖች ላይ ቢነሳም እርሱና ደጋፊዎቹ በእግዚአብሔር ክንድ በመቅሰፍት ተመትተው ይወድቃሉ፡፡ ንጉሡ እግዚአብሔርም በደብረ ዘይት ተራራ ጫፍ ይቆማል ይክፋት ኃይሎችም ፍጻሜ ያን ጊዜ ይሆናል፡፡ ዘካ 14፡4፡፡

# ዳግም ምጽአት

- ክርስቲያኖች  በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በደመና ሲመጣ   ያዩታል። “ ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቦአልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ።” ተብለናል። *ሉቃ 21፡27-28።*

- ጌታችን ራሱ ስለ ዳግም ምጽአቱ ተናግሯል። በግርማ መለኮት በቅዱሳን መላእክትም ታጅቦ የሚመጣ ስለመሆኑም በደቀመዛሙርቱ አሳስቦናል። “በዚህም በዘማዊና በኃጢአተኛ ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፥ የሰው ልጅ ደግሞ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ በእርሱ ያፍርበታል።” *ማር 8፡38፤ ማቴ 16፡27፤ ሉቃ 12፡40፤ ዮሐ 14፡3፤ ሥራ 1፡11፤ ይሁዳ 14-15፤ 1ኛ ዮሐ 2፡28፤ 1ኛ ጴጥ 4፡13፤ 1ኛ ቆሮ 4፡5፤ 1ኛ ተሰ 5፡2-6*… ።

- ዳግም ምጽአቱ ድንገተኛ እንደሆነ “መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤ … የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ።” በማለት ነግሮናል። *ማቴ 24፡27-30።*

- በማስከተልም የሰው ልጅ እልፍ አእላፍ በሚሆኑ መላእክቱ በክብር ታጅቦ በግርማው ይገለጣል። “፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል” *ማቴ 24፡27-30።* አመጣጡም በትሕትና እንደ ድሃ ሆኖ ራሱን ከገለጠበት ከመጀመሪያው ዓይነት ይለያል። መጀመሪያ የመጣው ነፍሱን ስለብዙዎች አሳልፎ ሊሰጥ ቢሆንም ዳግመኛ ግን በዓለሙ ሁሉ ሊፈርድና ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ሊከፍለው ይመጣል። “ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ” እንዳለ። *ራእ 2፡23፤ ሥራ 17፡31።*

# የሙታን ትንሣኤ

- ጌታችን ዳግም በሚመጣበት ቀን ሙታን ሁሉ ይነሣሉ:: "በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ::" እንዳለ:: *ዮሐ 5:29::*

- ሰዱቃውያን የሰው ልጆችን ትንሣኤ በመጠራጠራቸው የተነሳ ጌታችን "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ::" ብሎአቸዋል:: *ማቴ 22:29::*

- ቅዱስ ጳውሎስም የሙታን ትንሣኤ እንዳለ ስለማመናችን ጥቅም ሲያስረዳን "ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣማ፤ ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፤ ደግሞም፦ ክርስቶስን አስነሥቶታል ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለ መሰከርን ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል፤ ሙታን ግን የማይነሡ ከሆነ እርሱን አላስነሣውም:: ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣማ፤ ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ:: እንግዲያስ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ ጠፍተዋላ:: በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን:: አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል:: ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና:: ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና::" በማለት ጽፎልናል:: *1ኛ ቆሮ 15:13-22::*

- መልካም ያደረጉ ለክብር ኃጢአተኞችም ለፍርድ ይነሣሉ:: *ዮሐ 5:29፤ ሥራ 24:15::* "በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ::" *ማቴ 13:43::*

# የሙታን ትንሣኤ …

- ከትንሣኤም በ|ላ ባለው ሕይወት በአዲሱ ሰውነት ከማንኛውም ዓይነት የሰውነት ድካም ዛሬ ከሚታየው የአካል ዝለት ሁኑ ነጻ እንሆናለን፤ ሰውነታችንም መብልና መጠጥንም የማይሻ የማይራብና የማይጠማ ይሆናል፡፡ "ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።" እንዳለ፡፡ 1ኛ ቆሮ 15፡53፡፡

- ቅዱስ ጳውሎስም በሙታን ትንሣኤ ስለሚሆነው የሰውነታችን መለወጥ "ነገር ግን ሰው ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል። አንተ ሞኝ፥ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም፤ የምትዘራውም፥ ስንዴ ቢሆን ከሌላም ዓይነት የአንዱ ቢሆን፥ ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም፤ እግዚአብሔር ግን እንደ ወደደ አካልን ይሰጠዋል ከዘሮችም ለእያንዳንዱ የገዛ አካሉን ይሰጠዋል።" በማለት ያለንን እምነታችንን እንድናጠነክር ጽፎልናል፡፡ 1ኛ ቆሮ 15፡35-38፡፡

- በጌታችን ዳግም ምጽአት በምድር እየኖሩ የተገኙም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ተለውጠው እንደተነሡት ሙታን ይለወጣሉ፡፡ "እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን። ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።" 1ኛ ቆሮ 15፡51-53፡፡

- በመጨረሻም ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ያመኑበት ወዳጆቹ ከጌታችን ጋር ይገናኛሉ፡፡ "ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና። በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤ ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።" 1ኛ ተሰ 4፡13-17 ፤ ማቴ 24፡21-22፡፡

# የቁሳዊው ዓለም ማለፍ

- ሰው በኃጢአት በመውደቁ የተነሳ “ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና።” ሮሜ 8፡22።

- ነገር ግን የሰው ዘር ሁሉና አሁን የምንኖርበትም ቁሳዊ ዓለም የሚታደስበትና የሚነጻበት ዘመን ይመጣል። ይህም በመጨረሻው ቀን የመጨረሻውን ፍርድ ተከትሎ በእሳት አማካይነት ይሆናል። ከጥፋት ውሃ በፊት የነበረው ዓለም በጥፋት ውሃ እንደጸዳ ሁሉ አሁን ያሉት ሰማይና ምድር ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳስተማረን በእሳት ይጠፋሉ።

- ቅዱስ ጴጥሮስ “አሁን ያሉ ሰማያትና ምድር ግን እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል።.. ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል። የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፥ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይቀልጣል፥ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል። ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ፥ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኰላችሁ፥ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይፈታል፤ ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።” እንዳለ። 2ኛ ጴጥ 3፡7-13።

- ይህ ዓለም አላፊ እንደሆነም ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ “አቤቱ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው። እነርሱ ይጠፋሉ፥ አንተ ግን ትኖራለህ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፥ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፥ ይለወጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም። የባሪያዎችህም ልጆች ይኖራሉ፥ ዘራቸውም ለዘላለም ትጸናለች።” በማለት የዓለም ፍጻሜ ውድመቷ ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ መታደሷ እንደሆነ ገልጦልናል። መዝ 102፡25-27።

# የመጨረሻው ፍርድ

- ስለመጨረሻው ፍርድ ከተጻፉት ማቴዎስ በወንጌሉ *ማቴ 25፡31-46* የገለጠው የበለጠ አስረጅ ነው፡፡ “የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል፡፡ ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፡፡ … በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፡፡…” *ዮሐ 5፡22-29፤ ማቴ 16፡27፤ ማቴ 7፡21-23፤ ማቴ 11፡22-24፤ ማቴ 12፡35-42፤ ማቴ 13፡37-43፤ ማቴ 19፡29-30፤ ማቴ 25፡31-46፤ ሥራ 17፡31፤ ይሁዳ 14-15፤ 2ኛ ቆሮ 5፡10፤ ሮሜ 2፡5-7፤ ሮሜ 14፡10፤ 1ኛ ቆሮ 4፡5፤ ኤፌ 6፡8፤ ቆላ 3፡24-25፤ 2ናተሰ 1፡6-10፤ 2ኛ ጢመ 4፡1፤ ራእ 20፡11-15፡፡*

- ከላይ ከተጻፉት እንደምንረዳው የመጨረሻው ፍርድ በሙታንና በሕይወት ኖረው በሚገኙት በጻድቃንና በኃጥአን በሰይጣንና በሠራዊቱም ላይ ይደረጋል፡፡

- ፈራጁ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮታዊ ግርማው በቅዱሳን መላእክቱ ታጅቦ በዙፋኑ ሆኖ በዓለሙ ሁሉ ላይ ይፈርዳል፡፡ ኃጥአን “ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ፡፡” *ሮሜ 2፡5፡፡* እንደተባሉ ያ ቀን ምን ያህል የሚያስፈራ ነው? ይህ ፍርድ እውነተኛና የሁላችንም መጨረሻ የሚወሰንበት ፍርድ ነው፡፡ ኃጥአንንም “እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ…” ይላቸዋል፡፡ እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ፡፡

- በመጽሐፍ ቅዱስ ኃጥአን የሚገቡበትም ይህ ሥፍራ ለሰይጣንና ለመላእክቶቹ የተዘጋጀው ገሃነም፤ የእሳት ባሕር ነው፡፡ *2ኛ ተሰ 1፡8፤ ራእ 19፡20፤ ማቴ 25፡41፡፡*

# የማታልፍ መንግሥት

- ይህ ዓለም ሲያልፍ ዘላለማዊቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ትመጣለች። ምድራዊትዋ የፀጋው ግምጃ ቤት የሆነችው ቤተክርስቲያን ከማታልፈው የእግዚአብሔር ሰማያዊ መንግሥት ጋር ትዋሐዳለች። የእግዚአብሔር ልጅ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ብቻውን ገዥ ይሆንባታል። "ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።" ሉቃ 1፡33።

- ሞትም በጻድቃን ላይ ኃይሉን ያጣል። "የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፤ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል።" እንደተባለ። 1ኛ ቆሮ 15፡26 እና 54።

- "አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። … " ራእ 21፡1-። "ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፥ ከእንግዲህም ወዲህ አይጠሙም፥ ፀሐይም ትኵሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸውም።" ራእ 7፡16-17፤ ኢሳ 64፡4፤ 1ኛ ቆሮ 2፡9፤ እንዳለ ሁሉ አዲስ ይሆናል።

- ጌታችን "በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና…" እንዳለ ዮሐ 14፡2፤ 1ኛ ቆሮ 3፡8፤ 1ኛ ቆሮ 15፡41። በምድር ያመኑበትን በመንፈሳዊው ዓለም ባዘጋጀው ሥፍራ ያኖራቸዋል።

# ማጠቃለያ

- በርካታ ክርስቲያኖች የመጨረሻው የፍርድ ቀን ሩቅ ስለሚመስላቸው፤ የማይሆንም አድርገው ስለሚገምቱ በግድ የለሽነትና በኃጢአት ይኖራሉ፡፡

- ከመጨረሻው ፍርድ አስቀድሞ በርካታ መለኮታዊ ፍርዶች በየጊዜው እንደሚሰጡብን በማስታወስ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ማሻሻል ይኖርብናል፡፡ አዎ! መለኮታዊ ፍርድ በተናጠል በሰዎች፤ በቦታዎች ይልቁንም በመላው ዓለምም ላይ እንደተሠጠ የሚያረጋግጡልን ታሪኮች አሉ፡፡ እንደ ምሳሌም የኖኅ ዘመን የውሃ፤ የሰዶምና የገሞራ ጥፋቶች፤ የጥንታውያኑ የአሦር፤ የባቢሎን፤ የሮማ መውደቅ…ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ እኛም ከክርስቲያናዊ ሕይወት ከተለየን ከእግዚአብሔር ፍርድ የማናመልጥ መሆናችንን ማስታወስ ይኖርብናል፡፡ *ማቴ 24፡28፡፡*

- ባለቤቱ መቼ እንደሚመጣ ስለማናውቅ የመንፈሳዊ ሕይወታችንን ጉዳይ ዘወትር የምንከታተልና የሃይማኖታችንም ሻማ ሳይጠፋ ነፍሳችንንም በንጽሕና እንደጠበቅን መበርታት ይኖርብናል፡፡

- በዘመነ ሐዋርያት የጌታችን ወደ ዚህ ዓለም መምጣት አስፈላጊያችን እንደነበረ ሁሉ አሁንም ዳግም መምጣቱ አስፈላጊያችን ነው፡፡ በዳግም ምጽአቱ በዓለማችን ያለው ወንጀልና ወንጀለኝነት፤ የስህተት አሠራርም ሁሉ ያከትምለትና አዲስ ሕይወት በአዲሲቱ ዓለም እንኖራለንና፡፡

# ማጠቃለያ...

- ለዓለም ፍጻሜ ምልክት ሆነው ከተገለጹት የተፈጸሙትን መጥቀስ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህም፡-
   1. የብርሃን ወንጌል በዓለም ሁሉ መሰበክ
   2. እጅግ በተፋጠነ መልኩ ሰዎች ከእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን መውጣታቸውና መለየታቸው
   3. አይሁድ ወደ ጌታችን መመለሳቸው
   4. የሐሰተኞች ነቢያትና የሐሰተኛ ትምህርቶች መስፋፋት
   5. የሥነምግባር ደረጃ ዝቅ ማለት፤ የአስፈሪ ወንጀሎች፡ ጥንቆላና ሰይጣናዊ አሰራሮች መበራከት

- *ኢሳ 3፡9፡፡* "የፊታቸውም እፍረት ይመሰክርባቸዋል እንደ ሰዶምም ኃጢአታቸውን ያወራሉ፥ አይሠውሩአትም፡፡ በራሳቸው ላይ ክፉ ነገርን ሠርተዋልና ለነፍሳቸው ወዮ!" እንደተባለው ዛሬ ግብረ ሰዶማዊነትን፤ ጽንስ ማስወረድን ደግፈው ሰልፍ የሚወጡትን መመልከት በዛሬዋ ዓለም እንግዳ ነገር አይደለም፡፡

- ነውጠኝነት የሚታይባቸው ሙዚቃዎችና ፊልሞችም ምጽአቱን የሚያስታውሱን ናቸው፡፡

- እነዚህን ሁሉ ብንመለከትም ዓለም የሚፈጸምበትን እርግጠኛውን ጊዜ መናገር አንችልም፤ ከእግዚአብሔር በቀር የሚያውቀው የለምና፡፡

*መሐሪው አምላካችን እግዚአብሔር በሚመጣው የፈተና ጊዜ ሁሉ ጠብቆ በመልካሙ ጎዳና ይምራን፡፡ አሜን፡፡*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ይቆየን።